# ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከል ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማሸጋገሪያ መመሪያ

ትምህርት ሚኒስቴር

ታህሳስ 2000 ዓ.ም

*ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከል ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ማሸጋገሪያ መመሪያ*

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሙያ ብቃት፣ የሥራ ተነሳሽነት፣ በየጊዜው ራሱን ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ጋር የሚያስማማ እንዲሁም የኢኮኖሚ ዕድገትንና ልማትን የሚያፋጥን የሰው ኃይል በማፍራት ለሥራ ገበያው የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት ምላሽ የመስጠት ተቀዳሚ ተግባር ያለው ቢሆንም፤

የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ መሠዊና አካዳሚያዊ ብቃቱ ያላቸውን ግለሰቦች አካዳሚያዊ እድገት የሚያ መሆን ስለሚኖርበት ትምህርት ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማእከ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማሸጋገሪያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

2.1 የቴ/ሙያ ትም/ሥልጠና ዋና ተግባር በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማፍሪያ መሆኑን ተግባራዊ ማድረግ፣

2.2 ከቴ/ሙያ ትም/ሥልጠና ተመራቂዎች መካከል ብቃቱ ያላቸው ሰልጣኞች ብቻ ወደ ከፍተኛ ትምህርት መቀጠል የሚችሉበትን ሥርዓት ማዘርጋትና ዋና መስፈርቶችን ማሳወቅ፣

2.3 የቴ/ሙያ ትም/ሥል/ሥርዓት ከከፍተኛ ትምህርት ስርዓት ጋር የሚኖረውን ዓምዳዊ ትሥሥር በግልጽ ማሳየት፣

## 3. ትርጓሜ -

በዚህ መመሪያ መሠረት

3.1 "የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና" ማለት በምንዳ ተቀጥሮ ወይም ሥራን ፈጥሮ ራስን ለማኖር የሚያስችል ብቃት ለመላበስና በአንድ የሙያ ማእከ ክህሎትን፣ ዕውቀትንና የሥራ ባህርይን ለመቅሰም የሚሰጥ የትምህርትና ሥልጠና መርሐግብር ነው፡፡

3.2 "የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ብቃት ማዕቀፍ" ማለት የአንድን ሙያ የብቃት ሥልት፣ ጥልቀትና ወሰብሰብነት፣ ብቃቱ የሚጠይቀውን የኃላፊነት መጠንና በሥራ ላይ ራስን የማኖር ነፃነት፣ የሥራን ሁኔታ ወሰብሰብነት፣ ትሥሥር፣ ግልፅነት፣ እና ተለዋዋጭነት ከግንዛቤ በማስገባት የሙያዎችን የበቃት ደረጃ የሚያስቀምጥ ሰነድ ማለት ነው፡፡

3.3 "ወደ ከፍተኛ ትምህርት ማሸጋገሪያ (Pathways to Higher Education)" ማለት የሀለተኛ ደረጃን የመጀመሪያ እርከን ያጠናቀቁ፣ ለሙያ ምዘና ፈተና በመቀመጥ ብቃታቸው የተረጋገጠላቸው፣ በሙያቸው ቢያንስ ሁለት ዓመት የሠሩና የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተናን በመወሰድ ትምህርት ሚኒስቴር በሚወስነው የማለፊያ ነጥብ መሠረት አልፈው የሙያ ምዘና ባለፈበት የሥልጠና ማእከ የመጀመርያ ዲግሪ ፕሮግራም የሚከታተሉበት መተላለፊያ ነው፡፡

3.4 “የሙያ ደረጃ” ማለት አንድ ሠልጣኝ በአንድ የሙያ መስክ ለመሥማራት ይችል ዘንድ ሊኖረው የሚገባውን የሙያ ብቃት ዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው፡፡ የሙያ ደረጃ ምደባ የግለሰብን ብቃት ወይም ግለሰቡ የሠለጠነበት ሥርዓተ ትምህርት የሚገመገምበት የደረጃ መለኪያ ነው፡፡

3.5 “የሙያ ብቃት ምዘና” ማለት አንድ ሰው በአንድ የተወሰነ የሙያ መስክ የቴክኒክና ሙያ ብቃት ያለው መሆኑን ወይም ያለመሆኑን ለማረጋገጥ በሙያ ደረጃ ላይ ተመሥርቶ ምዘና የሚከናወንበት ሥርዓት ሲሆን፣ ይህም አገር አቀፍ ዕውቅና ያለው የቴክኒክና ሙያ ብቃት ምስክር ወረቀት ለማግኘት ቅድመ ሁኔታ ይሆናል፡፡

3.6 “የሙያ ምዘና ማዕከል” ማለት በክልል ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አካላትና በግሉ ዘርፍ ሥር የተዋቀረ ማዕከል ሲሆን የክህሎት ምዘናን በሚደራጅትና በሚከናወን የተሠማራ እንዲሁም ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓቱ የአቅም ግንባታ፣ የምክርና የምርምር አገልግሎት የመሳሰሉትን ሙያዊ ተግባራት የሚያከናውን ማዕከል ነው፡፡

3.7 “የማካካሻ ትምህርት (Bridging Course)” ማለት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምሩቃን ለዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና ለመዘጋጀት በመሰናዶ ትምህርት ላይ ተመሥርቶና በሞጁል (Module) ተዘጋጅቶ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

3.8 “የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና” ማለት ከመሰናዶ የማካካሻ ትምህርት ዝግጅት በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት የሚሰጥ አገር አቀፍ ፈተና ማለት ነው፡፡

## 4. የቅበላ መስፈርቶች

በዚህ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ያሟሉ አመልካቾች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ገብተው የሙያ ምዘና ባለፉበት የሙያ መስክ ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡

4.1 በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት 10ኛ ክፍልን (በቀድሞው 12ኛ ክፍልን) ስለማጠናቀቃቸው ማስረጃ የሚያቀርቡ፣

4.2 የሥራውን ዓለም ፍላጎት መሠረት በማድረግ ከተዘጋጀው የሙያ ደረጃ /Occupational Standard/ በመነሣት የሚዘጋጀውን አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና በመውሰድ ከፍተኛውን ወጤት ያስመዘገቡ፣

4.3. ለሙያ ምዘና በተፈተኑበት ሙያ ሕጋዊ የሁለት ዓመት ተግባራዊ የሥራ ልምድ ማስረጃ የሚያቀርቡ፣

4.4 ኃላፊነት በተሠጠው አካል በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጀውን የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ወስደው /Entrance Exam/ ያለፉ፣

## 5. የአስፈፃሚ አካላት የስራ ድርሻና ሃላፊነት

በቴ/ሙ/ት/ሥ እና በከፍተኛ ትምህርት መካከል የመሸጋገሪያ መሠላል በመፍጠር ዜጎች የሙያ ብቃታቸውን ማሻሻል የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት ረገድ ይህ መመሪያ ጉልህ ድርሻ ያለው ሲሆን ለተግባራዊነቱም

የበርካታ ባለድርሻዎች አስተዋጽኦ ወሣኝ ነው፡፡ ከእነዚህ አስፈፃሚ አካላት መካከል ትልቅ ድርሻ ያላቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

## 5.1 ትምህርት ሚኒስቴር

5.1.1 የምዝገባና የፈተና ወቅቶችን ያሣውቃል

5.1.2. ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ብቁ የሆኑትን እጩ ተፈታኞች ይመዘግባል፣ ይፈትናል፣ ወጤቶቻቸውንም ያሳውቃል፡፡

5.1.3. የከፍተኛ ትምህርት የመግቢያ ነጥብን በየወቅቱ ይወስናል፡፡

5.1.4. የመሸጋገሪያ ማካካሻ ትምህርት (Bridging Course) ይዘትን /Content/ ያዘጋጃል፡፡

5.1.5. የሙያ ብቃት መመዘኛ /Assessment Tools/ ያዘጋጃል፤

5.1.6. የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምዘና የሚሠጡ ባለሙያዎችን /Assessors/ እና የሙያ ብቃት መመዘኛ አዘጋጆችን /Assessment tools developers/ ያሠለጥናል፡፡

## 5.2. የክልል ት/ቢሮዎች /የቴ/ሙ/ት/ስ ኤጀንሲዎች/ ኮሚሽኖች

5.2.1 በክልሉ ወስጥ ባሉ የብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት (Center of competence) አማካኝነት የሚሠጠውን የሙያ ብቃት ምዘናና የምስክር ወረቀት አሠጣጥ ሂደትን በበላይነት ይመራል፡፡

5.2.2 የሙያ ብቃት ምዘናውን ወጤት በየወቅቱ ለትምህርት ሚኒስቴርና ለሚመለከታቸው ሌሎች ክፍሎች ያሣውቃል፡፡

## 5.3 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማዕከላት

5.3.1 የሙያ ብቃት ምዘና የሚሰጥባቸውን የሙያ ዓይነቶችን ለይተው ይገልፃሉ፤

5.3.2 ለፈተናው ብቁ የሆኑትን እጩ ተፈታኞች መረጃዎችን አጣርተው ለፈተና ብቁ የሆኑትን ይመዘግባሉ፡፡

5.3.3 ምዘናውን ለማካሄድ የሚያስችል ጥሩ አደረጃጀትና በቂ የመፈተኛ መሣሪያዎች ላላቸው ተቋማት፣ ድርጅቶች፣ ፋብሪካዎች፣ ወዘተ በመስፈርት እውቅና ይሠጣሉ፡፡

5.3.4 እውቅና ባገኙ የምዘና ማዕከላት /Testing Centers/ ምዘና ያካሂደሉ፡፡

5.3.5 የሙያ ብቃት ምዘናውን ላለፉ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ዝርዝሩቸውን ካገኙት ነጥብ ጋር ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያስተላልፋሉ፡፡

5.3.6 በደንብና መመሪያ መሠረት ለሚሰጡ የሙያ ብቃት ምዘና ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላሉ፡፡

## 5.4 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

5.4.1 የተዘጋጀውን የመሸጋገሪያ ማካካሻ ትምህርት (Bridging Course) መሠረት በማድረግ ሚስጢራዊነታቸውን በጠበቀ ሁኔታ የመግቢያ ፈተናዎችን በጋራ ያዘጋጃሉ ወይም በሚወክሉት አካል አማካኝነት እንዲዘጋጅ ያደርጋሉ ፡፡

5.4.2 የተዘጋጁትን ፈተናዎች ፈተናዎችን ለሚያስተዳድረው አካል በወቅቱ ያስረክባሉ፡፡

## 6. ከተማሪዎች ስለሚጠበቅ ሁኔታ

6.1 ተዘጋጅቶ በቀረበው የማካካሻ ትምህርት ይዘት መሠረት ራሳቸውን ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ያዘጋጃሉ ፡፡

6.2 በደንብና መመሪያ መሠረት ለፈተናው የሚፈለግባቸውን ክፍያ ይፈጽማሉ፡፡

6.3 ፈተናውን በብቃት ያለፉ ተማሪዎች በማግኘት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብቶ መማር መቻሉን ያለመሆኑ በመረዳት የራሳቸውን አማራጭ መንገዶች ያዘጋጃሉ፡፡

## 7. የማካካሻ ትምህርት (Bridging Course)

የማካካሻ ትምህርት ሰልጣኞች ቀደም ሲል ባለፉባቸው ትምህርትና ሥልጠናዎች ያልተማሯቸውን ዩኒቨርስቲ ገብተው የከፍተኛ ትምህርታቸውን ለመከታተል የሚያስችሏቸውን እንዲሁም የአካዳሚው ዕውቀት ሊጨብጡ የሚያስችሏቸውንና ለብሔራዊ ፈተና የሚያዘጋጃቸውን የትምህርት ዓይነቶችና ይዘቶችን የሚያካትት ነው፡፡ የማካካሻ ትምህርት ማጠናቀቂያ ማስረጃ ማቅረብ ግዴታ ባለመሆኑ ተማሪዎች የማካካሻ ትምህርትን ባመቻቸው መንገድ /በማታ፣ በርቀት፣ በራስ ጥናት ወዘተ…/ ተምረው ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡

## 8. የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና

8.1 በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፈተናዎች ኤጀንሲ አስተባባሪነት በሚመለከታቸው ዩኒቨርስቲዎች ወይም ተወካያቸው የመሸጋገሪያ ትምህርትን (Bridging Course) መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅና በብሔራዊ ደረጃ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ለዚህ ፈተና የተቀመጡት ተፈታኞች በፈተናው ያገኙትን ውጤት የሚገልጽ የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሲሆን የማለፊያ ነጥቡ በየወቅቱ በትምህርት ሚኒስቴር የሚወሰን ይሆናል፡፡ ተፈታኞች ለዚህ ፈተና ባመቻቸው መንገድ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

8.2 በአንድ የትምህርት ዘመን የተገኘ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ውጤት ከሶስት ዓመት በኋላ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት አያገለግልም፡፡

8.3 ማንኛውም ለከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና የሚቀመጥ ተፈታኝ ለመግቢያ ፈተናነት የተቀመጡትን ሁሉንም የትምህርት ዓይነቶች በአንድ ጊዜ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

8.4 የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና ውጤት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመግባት የሚያገለግለው ለአንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡

## 9. ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

9.1 ከዚህ ቀደም ከግብርና ማሰልጠኛ ተቋማት በዲፕሎማ ተመርቀው የወጡ ተማሪዎች ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሸጋገሩበት መመሪያ በሥራ ላይ ይቆያል፡፡

9.2 ከላይ በተራ ቁጥር 9.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማንኛቸውም መመሪያዎች ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 10. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ታህሣሥ 19 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር